צבא ההגנה לישראל | משרד הביטחון | האגף הביטחוני חברתי



## ለደኅንነት  አገልግሎት  ተወዳዳሪዎች መልዕክት(ለደኅንነት አገልግሎት የታቀደ) እና ለቤተሰቦቹ

እኛ ከኢትዮጵያ  ወደ እስራኤል ተመልሰን  በምደሪቱ  ተቀማጭ የሆንን ጺዮናዊ__ህልማችን  ግብ  ላይ ለማድረስ በቅተናል፡፡ ዛሬ ወንድና ሴት  ልጆቻችሁ ህልማችሁን በመቀጠል በእስራኤል የመከላከያ ጦር ወደፊት ያገለግላሉ፡፡

ለልጆችሁ  የምልመላ  ሂደት ሙሉ ተሳታፊዎች  እንደሆናችሁ እናያለን፡፡ ለእናንተ ለወላጆችና  ለልጆቻችሁ ቀላል እንዲሆንላችሁ ልጆቻችሁ  በአስራኤል መከላከያ ጦር ስለሚያገለግሉበት  ሁኔታ  ዕርዳታን አስመልክቶ (ያገልግሎት ሁኔታ) ይህች ወረቀት  መልዕክት ይዛላችሁ  ቀርባለች፡፡




תשלומי משפחה 1

אישורים נדרשים 3 ማመልከቻውን ለመገምገም የሚጠየቁ መረጃዎች

חייל נשוי 5 ለባለትዳር ወታደር

חייל בודד 6 ብቸኛ ወታደር

הטבות כספיות 7 የገንዘብ ዕርዳታ

הטבות דיור 8 የመኖሪያ ጠቀሜታዎች

הקלות בתנאי שירות 9 አገልግሎት እንዲቃለል የሚያስችሉ ሁኔታዎች

בן יחיד 10 አንድያ ልጅ

דמי כלכלה לטבעוניים 11 ተፈጥሯዊ ተመጋቢዎች ወጭ የሚሰጥ








ለግለሰቡ የመመልመልያ ክፍል ለእጩ ተመልማይ ጉዳይ እንክብካቤ ኃላፊ(ለደኅንነት አገልግሎት እጩዎች) ለእስራኤል ወታደራዊ አገልግሎት ተመልማዮችን የገንዘብ፣ የማኅበራዊና ቤተሰባዊ ችግሮች የዕርዳታ አማራጮችንና ምላሽ መስጠትን በተመለከተ ይሆናል፡፡ ወደ ግለሰብ የምልመላ ክፍል ለምልመላ እጩ ልጃችሁን ለቃለ መጠይቅ ይጋበዛል፡፡

እንደሚገባው በችግሮቻቸው ተገቢ እንክብካቤ እንዲደረግላቸው አስፈላጊ መረጃዎችን ሁሉ ከወዲሁ በማዘጋጀት ለቃለ መጠይቅ በተቀጠረላቸው ጊዜ መቅረብ አስፈላጊ መሆኑን እንድታውቁ ያስፈልጋል፡፡

## ለቤተሰብ ክፍያዎች - תשלומי משפחה

ልጆቻቸው ለውትድርና ለሚመለመሉ ቤተሰቦች ለመስተዳደሪያ እንዲሆን ተብሎ(እንደ ገቢ ማሟያ) አገሪቱ ህግ በሚል መልክ ለቤተሰብ ክፍያዎች ይሰጣል፡፡

የቤተሰብ ክፍያው ማመልከቻ የቤተሰቡ ጠቅላላ ገቢ ከተገመገመ በኋላ ማመልከቻው ተቀባይነት ሲያገኝ ለቤተሰቡ ወርሃዊ ዕርዳታ መብት ይሰጣል፡፡

**ለሁለቱ ወላጆቻችህ ማመልከት ትችላለህ፣ ወይም ለአንዱ፡፡ ያገባህ ከሆነ በባለቤትህ ልጅ ካለህ ለአንድ ልጅ ወይም ከዚያም በላይ ለልጆች ማመልከት ትችላለህ፡፡**

የቤተሰብ ክፍያዎች በቀጥታ ወደ ወላጆች ወይም ወደ ትዳር ጓደኛው የባንክ ሂሣብ ይተላለፋሉ፡፡

**<u>ማመልከቻውን ለመገምገም  የሚጠየቁ መረጃች፡</u>  - <u>אישורים נדרשים</u>**

**ሀ. የ3 ወራት  የወላጆች/የትዳር ጓደኛ የደመወዝ መቀበያ ቅፅ(እንደ ጥያቄው ዓይነት)**

**ለ. የወላጆች/የትዳር ጓደኛ የ3 ወራት  የ60 ተከታታይ ቀናት የባንክ ዝርዝር(እንደ ጥያቄው ዓይነት)**

ሐ. ከቢጡዋህ ልዑሚ የድጎማ ክፍያ ካሉ - **የ3 ወራት**

መ. ከወላጆች የአንዱን መታወቂያ የልጆችን ዝርዝር ጭምር ፎቶኮፒ(ለቤቴሴብ ክፍያ)

ሠ. እንደ አስፈላጊነቱ የሞግዚትነት ፈቃድ

ረ. በራስህና  በቤተሰብህ/በትዳር ጓደኛህ የተሞላና የተፈረመበት የቤተሰብ ክፍያ ቅፅ(ቅፁን በመመልመያው/በቃለ መጠይቁ ማግኘት ይቻላል)

ሰ. በክሬዲት ካርድ  ጥቅም ዝርዝር

ሸ. (ጠቅላላ የተቀማጭ ገንዘብ የሚያሳይ የክሬዲት ካርድ ጥቅም ዝርዝር)

የቤተሰብ ክፍያ(የቤተሰብ ክፍያ) በቋሚ መመሪያዎች መሠረት የመሚታይ ሲሆን ወዲያውኑ መብት አይሰጥም፡፡





ለቤተሰብ ክፍያ የመቀበል መብት እንደሚደርስህ ከታወቅህ - የሚከተሉትን የዕርዳታ አማራጮችን ትቀበላለህ፡

ሀ. **<u>የድጎማ ክፍያ</u>** - ወላጆቹ የቤተሰብ ክፍያ መብት ላላቸው ቤተሰብ  ለሆነ ወታደር ከወታደር ከሚቀበለው ደመወዙ ጋር በየወሩ ይቀበላል፡፡

ለ. **<u>ለበዓል ቀን ለመግዣ የሚሰጥ</u>**- ወላጆቹ የቤተሰብ ክፍያ የመቀበል መብት ላላቸው ወታደር ለሆነ በየወሩ ከሚቀበለው ደመወዝ በዓመት ሁለት ጊዜ(በዓመቱ መለወጫና በፋሲካ) በ50 ሱቆች በበዓሉ ሊገዛበት የሚችል  መግዣ ሰነድ ይሰጠዋል፡፡

ሐ. <u>የወንድም  ድጎማ</u> - ለአገልግሎት ቅድመ ሁኔታ ክፍያ የሚቀበል የሚያገለግል ወታደር ወንድም ላለው ወታደር ወንድሙ እንደሚቀበለው ይቀበላል፡፡ በከፍተኛ አገልግሎት ለሚገን ወንድም መብቱን እንዲከበርለት እንገፋፋለን፡፡

መ. <u>ለምግብ መግዣ ገንዘብ የመቀበል መብት</u> - ወዲያውኑ ለሚቀበሉ ተዋጊ ወታደሮች በቀር ወታደሩ ከተመለመለ በኋላ የገንዘብ ችግሩ መጠን ይገመገማል፡፡









**ለባለትዳር ወታደር - חייל נשוי**

**በውትድና የግልጋሎት ዘመንህ እንደባለትዳር ከተቆጠርክ የሚከተሉትን ጥቅሞች መቀበል ትችላለህ፡**

ሀ. **የቤተሰብ ክፍያ** - በእስራኤል የመከላከያ ጦር የግዴታ አገልግሎት ላለ ወታደር በአንዳንድ ሁኔታዎች ለቤተሰብ የሚሆን ልዩ ክፍያ ይከፍላል፡፡

ለ. **በግዴታ አገልግሎት መካከል ለሚፈጸም ጋብቻ** - በግዴታ አገልግሎቱ ጊዜ ለሚያገባ ወታደር ከመደበኛው የዕረፍት ቀናት የሚታሰብ 10 የዕረፍት ቀናትና በልምምድ ለሚሰጠው ደመወዝ ሙጠን ለአንድ ጊዜ ክፍያና ከወታደር ድርጅት የዕቃ መግዣ የሚውል ሰነድ እንዲቀበል ይፈቀድለታል፡፡

ሐ. **የቤት ኪራይ/ቤት መያዣ ወጭዎች** - በኪራይ ቤት ለሚገኝ ወታደር ለቤት ኪራይ ወጭ ተሳትፎ እንዲደረግለት ማመልከት ይችላል፡፡ የመኖሪያ ቤቱ ተሳትፎ እንደማመልከቻው ሁኔታ ይታያል፡፡

መ. **በአገልግሎት ላለ ወታደር ልጅ በሚወለድበት ጊዜ** - ባለሙብቱ ወታደር በልምምድ ጊዜ በተቀበለው ደመወዝ መጠን ለአንዴ ብቻ ደመወዝና ለወታደሩ ከሚደርሰው መደበኛ ዕረፈት የሚታሰቡ ስምንት የዕረፍት ቀናት፣ እንሁም ከወታደሩ ድርጅት የመግዣ ሰነድ ይሰጠዋል፡፡



**ብቸኛ ወታደር - חייל בודד**

በእስራኤል የመከላከያ ጦር በአገልግሎታቸው ጊዜ የሚደግፋቸው(ወላጆቻቸው አገር ለቀው ለሄዱባቸው ፣ ብቻቸውን ወደ እስራኤል ለመጡ አዲስ ገቢዎች፣ ወላጃጆቻቸው ለሞቱባቸውና ከወላጆቻቸው ጋር ግንኙነት ለተቋረጠባቸው) ብቸኛ ወታደሮችን ይረዳል፡፡ ዕርዳታ ለሚያስፈልገው ብቸኛ ወታደር ካለ ወደ ወታደር መመልመልያ ክፍል ማመልከት ይኖርበታል፡፡ ማመልከቻው ከተገመገመ በኋላ በመኖሪያ አድራሻው ደብዳቤ ይላክለታል፡፡

**ማመልከቻው እንዲታይ የሚያስፈልጉ መረጃዎች፡**

**ሀ. ለመመልመል የታጨው ወታደር ራሱ አዲስ ገቢ መሆኑን - መረጃ አልባ**

**ለ. ለመመልመል የታጨው ወታደር ለአገልግሎት ወላጆቹ በውጭ ተልከው ከሆነ- መቼ አንደሚመለሱ የሚጠቅስ መረጃ ከላኪው ተቋም**

**ሐ. ለመመልመል የታጨው ወታደር ወላጆች አገረ ለቀው የሄዱ ከሆነ- ወላጆቹ ለምን አገር ለቀው እንደሄዱና የመመለስ ዕቅድ እንዳላቸው**

**መ. ለመመልመል የታጨው ወታደር ወላጆች ሟች መሆናቸውን- የወላጆች ሞት መረጃ**

**ሠ. ለመመልመል የታጨው ወታደር ከቤተሰቦች ጋር ግንኑነት መቋረጥ - የማኅበራዊ ሠራተኛ መረጃ ወይም ከታወቀ ማኅበራዊ ድርጅት በአማከሪ የታጀበ ማበረታቻ ደብዳቤ**

**ብቸኛ ወታደር እንደሆነ ዕውቅና ካገኘ ዕርዳታ ለመቀበል የሚከተሉት አማራጮች አሉት፡**

**<u>የገንዘብ ዕርዳታ</u> - <u>הטבות כספיות</u>**

ሀ. **<u>ወርሃዊ ድጎማ</u>** - በወታደሩ ከሚያገነው ደመወዝ በየወሩ ይሰጠዋል፤ ድጎማው በሥልጠና ጊዜ ከሚያገኘው 100% ነው፡፡

ለ. **<u>ለበዓል ጊዜ መግዣ</u> - ብቸኛ ወታደር** በዓመት ሁለት ጊዜ(በዓመቱ መለወጫና በፋሲካ) በ50 ሱቆች ሊጠቀምባቸው የሚችሉ መግዣ ሰነድ ይሰጠዋል፡፡

ሐ. **<u>ወላጆቹን ሂዶ እንዲጎበኝ የአየር ጉዞ ወጭን መሸፈን</u>** - ወላጆቻቸው ውጭ አገር የሚኖሩ ብቸኛ ወታደሮች ወላጆቻቸውን እንዲጎበኙ በአገልግሎታቸው ዘመን አንድ ጊዜ እስራኤል መከላለከያ ኃይል በወሰነው መመዘኛ ነጥቦች መሠረት ወታደራዊው ድርጅት የአየር ጉዞውን ወጪ በመሸፈን ይሳተፋል፡፡

መ. **<u>የምግብ ግብዣ የሚሆን የገንዘብ ዕርደታ</u>** - ልዩ ኢኮኖሚያዊ ችግር ለሚያቀርቡ ወታደሮች እስራኤል መከላለከያ ኃይል የምግብ መግዣ የሚውል የገንዘብ ዕርዳታ ያደርጋል፡፡ ዕርዳታ የመቀበል መብት ላለው በሀገሪቱ ባሉ "ሹፈር ሳል " ምግብ መግዛት የሚያስችል መግዣ በየወሩ ይሰጠዋል፡፡







**<u>የመኖሪያ ጠቀሜታዎች</u> - <u>הטבות דיור</u>**

ለመኖሪያ ቤት ዕርዳታ ለመቀበል የእስራኤል መከላለከያ ኃይል በወሰነው መመዘኛ ነጥቦች መሠረት ዓይነት ሲሆን አማራጮችም እነሆ፡

ሀ. **<u>የቤት ኪራይ</u>** - **ከ**እስራኤል መከላለከያ ኃይል የቤት ኪራይ ዕርዳታ ለመቀበል ወታደሩ ብቸኛ ወታደር መሆኑ ከታወቀ በኋላ ለቤት ኪራይ ቅናሽ ማመልከት ይችላል፡፡(ብቸኛ ወታደር የተባለ ሁሉ የቤት ኪራይ ቅናሽ የመቀበል መብት የለውም)፡፡ ለማመልከቻው ተቀባይነት እንዲያገኝ የቤት ኪራይ የተዋዋለበትን የመጀመሪያ ውል ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ማመልከቻው ተቀባይነት ካገኘ ውትድርና ከተመለመለበት ቀን ጀምሮ ቅናሽ የመቀበል መብት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ቤትን ለመያዝ የሚጠይቀውን ወጮች(እንደ ግብር፣ የውኃና የጋዝ) ቅናሽ የሚደርሰው ሆኖ ከተገኘ **የ**እስራኤል መከላለከያ ኃይል ይሳተፋል፡፡

ለ. **<u>ለብቸኞች ቤቶች</u>** - በአገሪቱ ተሰራጭተው በሚገኙ የወታደሮች ድርጅት ለወታደሮች በያዛቸው በዕቃና በተስማሚ ሁኔታ የተሞሉ ወታደሩ በውትድርና አገልግሎቱ ዘመን መደበኛ ሕይወቱን ማካሄድ የሚያስችሉ ቤቶች የመተኛት ዕድሎች አሉ፡፡ ወታደሩ የቤት ኪራይና ግብር እንዲከፍል አይጠየቅም፡፡

ሐ. **<u>ቂቡጾች ውስጥ ማደር</u>** - ለቂቡጾች እንቅስቃሴ የሆኑ በአገሪቱ ሁሉ በአሥሮች ቂቡጾች ይከናወናል፤ ዝግ በሆኑ የወታደር ክፍል ለሚያገለግሉ ወታደሮች ነው የሚፈቀድላቸው፡፡ ወታደሮች ቂቡጹ በሚሰጠው እንደ ልብስ ማጠብንና 150 ሸኬል የኪስ ገንዘብ የመሳሰሉት ወታደሮች ይታደላሉ፡፡

መ. **<u>በወታደር ቤቶች ማደር</u>** - በመላ አገሪቱ ተሰራጭተው በሚገኙ የወታደሮች ድርጅት ለወታደሮች በሆኑ በሚገኙ ቅሪያት ሸሞኒ፣ ቲቤሪያ፣ ኢየሩሳሌም፣ ሐይፋ፣ ቤኤር ሼቫ በእኒህ ተቋማት ሁሉ ወታደሩ የልብስ ማተብንና ምግብን ይቀበላል፡፡

## <u>አገልግሎት  እንዲቃለል የሚያስችሉ ሁኔታዎች</u> - <u>הקלות בתנאי שירות</u>

የአገልግሎት ሁኔታዎችን የማቃለል ዓላማ ለእስራኤል መከላከያ ኃይል ለሚለመሉ ወታደሮች ልዩ የቤተሰብ ችግሮች ላሏቸው ቤተሰቦች ተመልማዩ በልዩ ሁኔታ እንዲያገለግል የሚጠይቁ ሁኔታዎችን ለማቃለልና ለመርዳት፡፡ የሚፈቀደው የመቃለል መጠን እንደችግሩና እንደመመዘኛዎች ይወሰናሉ፡፡

ማመልከቻውን ለማየት የሚፈለጉ መረጃዎች፡

ሀ. የቤተሰቡ አባላት ወቅታዊ የሆነ የህክምና/የነፍስ የጤና ሁነታ

ለ. ዕዳ ካለ የዕዳ መረጃ

ሐ. የኢኮኖሚ መረጃዎች(የባንክ ዝርዝር፣ የወጪ ዝርዝር፣ የክሬዲት ካርድና ወ.ዘ.ተ)

መ. የወላጆች የደመወዝ መቀበያዎች

ሠ. ካለ የማኅበዊ ጉዳይ ሠራተኛ መረጃ

ረ. ማመልከቻውን ሊደግፍ የሚችል ማንኛውም መረጃ ሁሉ







## <u>አንድያ ልጅ</u> - <u>בן יחיד</u>

**ለወላጆቹ(ለሁለቱ ወይም ለአንደኛው) <u>አንድያ</u> ልጅ የሆነ በጦር ግንባሮችና በተዋጊነት እንዲያገለግል አይገደድም፡፡**
እንዲህ ቢባልም በተዋጊነት ለማገልገል የሚፈልግ አንድያ ልጅ ቢኖርና ወላጆቹም ቢስማሙ ወደ ምልመላ ክፍል ቀርቦ ወይም ያሊም ዓል ሜዲም በተባለው ድህረ ገፅ እንዲሁም በከተማዎች ባሉ አድራሻዎች ቅፁን በመሙላት በበጎ ፈቀደኛነት ለማገልገል ማመልከት ይኖርበታል፡፡ ማመልከቻው በከተማዋ በሚገኘው የወታደር ባለሥልጣን በህግ ጠበቃ ፊት በእሱና በወላጆቹ ይሞላል፡፡

ቅፆችን የማመልከቻዎችን እንክብካቤ እንዲሁም የከተማውን የወታደር ባለሥልጣን አድራሻ ወደ ምልመላው ክፍል በማመልከት ወይም በቀጥታ ያሊም ዓል ሜዲም ከሚለው ድኅረ ገፅ በቀጥታ ማግኘት ይቻላል፡፡

## ተፈጥሯዊ ተመጋቢዎች ወጭ የሚሰጥ - דמי כלכלה לטבעוניים

ከርዕዮተ ዓለም ወይም ከጤና አንጻር በተፈጥሯዊ ሕይወቱን የሚመራ ተመልማይ እጩ ተፈጥሯዊ ተመጋቢ ተብሎ እንዲታወቅ ለእስራኤል መከላለከያ ኃይል ማመልከት ይኖርበታል፡፡

ማመልከቻውን በምልመላው ቢሮ እንዲያቀርብ ይፈቀድለታል፡፡ ተፈጥሯዊ ተመጋቢነቱ ከተወሰነለት ለወጩ ክፍያ እንዲደረግልህ በተፈላጊ ምግቦች ራስህን አዘጋጅ፡፡

**ማመልከቻው እንዲታይ የሚያስፈልጉ መረጃዎች፡**

ሀ. በከተማዋ የወታደር ባለሥልጣን በጠበቃ ፊት ቀርቦ የተፈጥሮ ምግብ ተመጋቢ ሕይወት እንደሚያካሂድ መናገር
ለ. በምልመላው ቢሮ በምክትል ጀኔራል ፊት ቀርቦ መናገር
ሐ. የተፈጥሮ ምግቦች ተመጋቢ መሆንህን ከሚመለከትህ ክሊኒክ የቤተሰብ ዶክተር መረጃ
መ. ከክሊኒክ ምግብ አጥኚ(ዲታኒት) ቅፅ መረጃ





## በውትድርና በአገልግሎት ሂደት ያለ የገንዘብ ችግር ለሚያቀርብ ወታደር ሊሰጡት የሚችሉ ጠቀሜታዎች

**ሀ.** **የመዋጮ ገንዘብ መርጃ** - በከባድ የገንዘብ ችግር ላጋጠመው ወታደር የጦሩ ክፍል የወታደሮች ድርጅት ለወታደሮች ጋር በመተባበር በመዋጮ ከተሰበሰበው የመርጃ ገንዘብ ለመረዳት ለአግልግሎት ሁኔታ ቢሮ በማመልከት ይሆናል፡፡ ዕርዳታው በምግብ፣ መለስተኛ የግል ዕቃ፣ ልብስና አስፈላጊ የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ዘርፍ ይሆናል፡፡

**ለ.** **ለምግብ መግዣ የመቀበል መብት** - በዚህ ወረቀት እንደተገለጸው ነው፡፡

**ሐ.** የትዕዛዝ ስጦታ - ይህ ስጦታ ለወታደሩ ወይም ለቤተሰቡ ለአስቸኳይ የገንዘብ ችግር ይሰጣል፡፡

**መ.** **ብድር** - እንደ አስፈላጊነቱና የገንዘብ ችግሩ ከተጠና በኋላ ብድሩ ይፈቀዳል፡፡

**ሠ.** **ልዩ ዕረፍት** - በከባድና አስቸኳይ የገንዘብ ችግር ላጋጠመው ወታደር ወይም ለማንኛውም የግል ችግር ወይም ለሥራ ልዩ ፈቃድ የመጠየቅ መብት ሲሆን ያም የሚደርሱትን መደበኛ ዕረፍት(ጠቅላላ ልዩ የዕረፍት ቀናት ለዓመት አገልግሎት ከ30 ቀናት ያልበለጡ) በሙሉ ከተጠቀመ በኋላ መጠየቅ ይችላል፡፡

ረ. **ለግል ሥራ ፈቃድ** - የገንዘብ ችግር ያጋጠመው ወታደር የግል ሥራ ለመሥራት ከአገልግሎት በኋላ የግል ሥራ ለመሥራት ማመልከት ይችላል፡፡ የግል ሥራ ፈቃድ የሚሰጠው የውትድርና ክፍል አዛዡ ምክትል ጄኔራል ማዕረግ ያለው ሲፈቅድና ፈቃዶች ከተመረመሩና የሥራው ዓይነትና ወታደሩ የሚያገለግልበት ሁኔታ ከታየ በኋላ ነው፡፡

ሰ. **አስቸኳይ ብድር** - ቢያንስ የአንድ ዓመት የአገልግሎት ዘመን ያለው ወታደር በአገልግሎት ሁኔታ ባለሥልጣናት አማካይነት ፎርም ከሞላ በኋላ(ያለመረጃዎች) ብድር የመቀበል መብት አለው፡፡ የብድሩ መጠን እስከ 500 ሸኬል ይደርሳል፡፡ ብድሩ ከተወሰደ በመጪው ዓመት ከወታደሩ ወርሃዊ ደመወዝ በኩል ወርሃዊ ክፍያ ይመለሳል፡፡

ሸ. **"ቅጽበታዊ" ስጦታ** - የገንዘብ ችግር አለብኝ ሲል ላመለከተ ወታደር ስጦታውን ለመቀበል ማመልከት ይችላል፡፡ ስጦታው ሊሰጥ የሚችለው በዓመት እስከ ሁለት ጊዜ ሲሆን በእያንዳንዱ ብድር ከ150 ሸኬል መብለጥ የለበትም፡፡



## ለመደምደሚያ፣

**ትብብራችሁ በጣም ያስፈልገናል፤ ወላጆች ከልጆች ፊት ለፊት፤ ልጆቻችሁ ወደ ምልመላው ቀድመው በመጡ ቁጥር አገልግሎታቸው ላይ ተፅዕኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ ቤተሰባዊና ግላዊ ችግሮች ከመመልመላቸው በፊት ጥራት ያለው እንክብካቤ ይደረግላቸዋል፤ በመብታቸው ወደ ደረጃ ወደ ሚያደርሷቸው የውትድርና ክፍሎች እንዲመደቡ መፍትሄ ይሰጣቸዋል፡፡**

**ለእስራኤል የጦር ኃይል ምልመላ በፊት ግዴታ የሆነውን ክትትል ለመፈጸም ለግል ቃለ መጠይቅና አስፈላጊ መረጃዎችን ማምጣት ከእናንተና ከልጆቻችሁ የሚጠበቅ ትብብር ይሆናል፡፡**

**በምልመላው ሂደት የወላጆች መደመር ለአገልግሎቱ ሂደትም በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ለወታደሩ ጥሩ አገልግሎት እንዲሆንለት በብዙ ሙቀትና ፍቅር ማቀፍ ያስፈልጋል፡፡(ለትዕይንቶችና በሚየገለግልበት ክፍል ዕየሄዱ መጠየቅ)**



ግብ የሚመታ አገልግሎት ይሁን!

**ለማንኛውም ተጨማሪ ጥያቄ ለኢትዮጵያውያን መቀላቀል ተረኛ**
**በስልክ፡ 03-5690822**

האגף הביטחוני חברתי

משרד הביטחון

צבא ההגנה לישראל